

# +++ ዘኦርቶዶክስ ተዋሕዶ +++

## የዕለት እንጀራ የዐቢይ ጾም (፩ኛ)

[፫፻፷፪ኛው እንጀራ] ሳምንቱ - ዘወረደ የካቲት ፩ ፳፻፪



”ዘመቻ ነፍስ” - የተቀደሰው ታላቁ የጌታ ጾም ዛሬ ተጀመረ። ይበልጥ ወደ እግዚአብሔር <u>በንስሐና በቁርባን</u> የምንቀርብበት ወራት ያድርግልን፡ ፡

ጽድቅን
የሚራቡና
የሚጠሙ
ብፁዓን ናቸው፥
ይጠግባሉና።

ማቴዎስ ፮፡፲፮

**ማቅ ለብሼ በአመድም ላይ ሆኜ ስጾም እጸልይና እለምን ዘንድ ፊቴን ወደ ጌታ ወደ አምላክ አቀናሁ።**

ዳንኤል ፱፥፫

አያሌ ቀንም
አዝን ነበር
በሰማይም
አምላክ ፊት
እጾምና እጸልይ
ነበር።

ነህምያ ፩፡፬

## <u>በዚህ ቀን ከሚታሰቡት መካከል</u>

፻፶ አባቶች የመቅዶንዮስን ትምህርት ለመለየት በቁስጥንጥንያ ጉባኤ የተቀመጡበት ቀን

### <u>ለማወቅና ለማድረግ</u>

ከዛሬ ጀምሮ ዐቢይ ጾም ነው። ጾሙ ፶፭ ቀናትን ሲይዝ እነዚህም በቅደም ተከተል፤

፩) ጾመ ሕርቃል (ሙሴኒ) - ፲ቀን

፪) የጌታችን ጾም (ጾመ ኢየሱስ) - ፵ ቀን

፫) ሰሙነ ሕማማት - ፯ ቀን ናቸው።

ዐቢይ ጾም የየራሳቸው መጠሪያና ምክንያት ባላቸው በ፰ ሳምንታት (ከእሁድ እስከ ቅዳሜ) ይከፈላል። እነዚህም ከዛሬ ጀምሮ ዘወረደ፤ ከዛ ቅድስት ፤ከዛ ምኩራብ ፤ከዛ መጻጉዕ ፤ከዛ ደብረ ዘይት፤ ከዛ ገብር ኄር ፤ከዛ ኒቆዲሞስ፤ ከዛ ሆሳዕና (ሰሙነ ሕማማት የሚጀምርበት)።

ዘወረደ - ከጌታችን በቀር ከስማይ የወረደ(የመጣ) ወደሰማይም በሥልጣኑ የሚወጣ የለም።